# የራሷ እያረረ
# የሰው ስታማስል

ተፈጥሮ ቢሆንም ፣ መውደድና መጥላት
የገጠመን እኛ ፣ ወዳጅ ሲሏት ፣ ጠላት
ልቧ የማይገኝ ፣ ጋባዥ ለደምፍላት
የለዘበች ሰይጣን ፣ አቻ አልተገኘላት ።

ለውጥ ለውጥ ፣ ትላለች ፣ ሳትለወጥ እሷ
ቅቤ እየጠበሰች ፣ ባሳሳች ምልሷ
ልዩ አጀንዳ ይዛ ፣ ሸሸጋ ለራሷ
ለካስ ፣ ኬኛ ኬኛ ፣ ነበረ ጥንስሷ ።

ከወያኔ አትከፉም ፣ ብሎ ቢቀበላት
ከነ ግሳንግሷ ፣ ተሸክሞ ቢያዝላት
ሚሊዮን ፣ ልትሸውድ ፣ በጠባብ ጭንቅላት
እሷ ፣ ብቻ አዋቂ ፣ የሆነች መሰላት
          ፀበል አትወሰድ ፣ እምነቷ አይፈቅድላት
          አቶ እስራኤል ዳንሳ ፣ ምነው ብትደርስላት ።

እቺን ምናምቴ ፣ እቺን የወሬ ቋት
ገመዷ ቢረዝም ፣ መስሏት የለቀቋት
ፊት እየነሳችሁ ፣ ምናል ብታርቋት
ለኛም አታሳዩን ፣ በሸሻ ደብቋት ።

ኬኛ ኬኛ ፣ የምትል ፣ ሲመሽ ፣ በረሃን ዘግታ
የሰው ስጋ በልታ ፣ የሰው ደም ጠጥታ
የማትጠረቃ ፣ አታውቅ ከበሬታ
እንደ ለገጣፎ ፣ ዛሬም በሱሉልታ
ተነስታለች ዳግም ፣ የሌላት ይሉኝታ
          ይሄንንም አላውቅ ፣ ትለናለች ወጥታ
          አለልክ ተብታ ፣ ከቶ ፣ ማንን ፈርታ ።

እሳት ተቀጣጥሎ ፣ ባህርዳር መቀሌ
አንዴ ከኬኒያ ፣ አንዴ ከሱማሌ
የምታቶሶትስ ፣ የመንደር አለሌ
ምነው ፣ ሃይ የሚላት ፣ ጠፋ ሽማግሌ ።

የሰላም ያንድነት ፣ ፊታውራሪ ይመስል
ወሬ እያራገበች ፣ የምትል ፣ ጡል ጡል
የራሷ እያረረ ፣ የሰው ስታማስል
ታውደለድላለች ፣ ወጧ ፣ ያማረ ይመስል ።

ታዛቢው

March 15, 2019